ቁ - 1496
19/6/12


በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance


ቁጥር
Ref.No. 7/ኢ/1/2/77
ቀን
Date 17 የካቲት 2012

ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ:- <u>ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጥር 19/2012 በቁጥር መ30-5/732/15 የተጻፈልንን ደብዳቤ ይመለከታል</u>

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በርዕሱ በተገለጸው ደብዳቤ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን የውጭ ድርጅቶች ሆነው የራሳቸውን የውጭ ምንዛሪ በመጠቀም በመንግሥት የተለዩ/የሚለዩ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ ስለሚያስገቡበት ሁኔታ መመሪያ እንድናዘጋጅ ያሳወቀን መሆኑ ይታወቃል።

ስለዚህ በተሰጠን አቅጣጫ መሠረት የተዘጋጀውን 6 ገጽ መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ የላክንላችሁ መሆኑን እናስታውቃለን።

ከሰላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ገንዘብ ሚኒስቴር 2

<u>አባሪ፣</u>
- 6 ገጽ መመሪያ

<u>ግልባጭ፣</u>
ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን No. 2
Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመንግስት የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 62/2012

የካቲት 2012 ዓ/ም
ገንዘብ ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

Ethiopian Ministry of Revenues
Records & Documentation No. 2

የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመንግስት የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 62/2012

በአሁኑ ጊዜ ሀገራችን ያጋጠማት የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት ምክንያት መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የውጭ አቅራቢዎች በራሳቸው ገንዘብ እንዲያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ችግር ለማቃለል የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በተሰጠው ውክልና መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመጠቀም በመንግሥት የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 62/2012" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው
2. "ሸቀጦች" ማለት የውጭ አቅራቢዎች ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ በመጠቀም ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቧቸውን በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተለዩ/የሚለዩ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችን እና የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ይጨምራል፡፡
3. "የውጭ አቅራቢዎች" ማለት ሸቀጦችን ከራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ተጠቅመው በዘገየ ክፍያ ለማቅረብ ፍላጎታቸውን በመግለፅ የመወዳደሪያ ሀሳብ ካቀረቡት መካከል በዚህ መመሪያ የመወዳደሪያ መስፈርት መሰረት ተመርጠው ከሚኒስቴሩ ጋር ውል የሚዋዋሉ የውጭ ድርጅቶች ናቸው፡፡
4. "ቀጥተኛ ገገር" ማለት ሸቀጦችን በቀጥታ ከውጭ አቅራቢ ገዝቶ ስራ ላይ የሚያውል ድርጅት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ.2
Ethiopian Ministry of Revenues Records & Documentation No.2
Ethiopian ... Commission Records & Documentation No.1